# ወይ ነዶ ፤ወይ ነዶ ! ! !

የዘንድሮ ታጋይ ፤ ልክስክሶ ውሾ
ለደርግ ለሻብያ ፤ ማርገድ ይዟል ሙሾ
        ማልቀስ ካማራቸው ፤ እንደ እንቧይ ይፍረጡ
        ታሪክን አጣመው ፤ ዐይን ሳያወጡ
        ጎረቤት ሳይነኩ ፤ ሰው ሳይበጠብጡ ።

ለራስ እንደማዘን ፤ ለራስ እንዳያለቅስ
ተፈጥሮው ሆኖበት ፤ ማንዛረጥ መልከስከስ
ነጩን ጥቁር ብሎ ፤ ያዞ እንባውን ማፍሰስ
ወንጀለኛን አቅፎ ፤ ተበዳዩን መክሰስ ።

ጆሮዬ ጉድ ሰማ ፤ ታምር አየሁ ባይኔ
ለደርግ ለሻቢያ ፤ እስካሉለት ወይኔ
ፊት መንጩቱ አይቀርም ፤ ነገም ለወያኔ።

ባቋሙ ያልፀና ፤ የተውገረገረ
እንደ እስስት ፤ መልኩን እየቀያየረ
እንደ ውሮ በላ ፤ የትም እያደረ
        ባሸዋ ላይ ጎጆ ፤ እሱው በቀለሰ
        ሌላውን ይከሳል ፤ ቤቱ በፈረሰ ።

ታግሎ ላይታገል ፤ እየወላወለ
በሻቢያ ደጅን ፤ እየተጠለለ
በስራው ተጠልፎ ፤ በተፈነገለ
ጣቱን ይቀስራል ፤ እነ እከሌ እያለ ።

የድርጅት ቡፌ ፤ ቅልውጥ የለመደ
አመሉ የከፋ ፤ የተወላገደ
ባፍ ጁዶ እየመታ ፤ ሰው እየሸወደ
አድሜውን ይገፋል ፤ እያሸረገደ ።

ባገሩ ሰቆቃ ፤ ሸቅጦ ለማትረፍ
ባለተራ ሆኖ ፤ በተራው ለመዝረፍ
ተገንጣዩን አቅፎ ፤ ታጋዩን በማጉደፍ
አሉባልታ  አንግቦ ፤ ይላል እንገፍ እንገፍ ።

ታጋይን አዋርዶ ፤ አገርን አዋርዶ
ታሪክን አጣሞ ፤ በጀግናው ቀልዶ
ያልተጻፈ አንብቦ ፤ ያልነበረ ቀዶ
ለሱ ካተረፈው ፤ ሊበላ ነግዶ
አሸር ባሸር ዛሬም  ፤ ወይ ነዶ ፤ወይ ነዶ ! ! !

ታዛቢው ... March 03,2012